# <u>አለም አቀፍ ጥበቃ ህግ 2015</u>

**[በአለም አቀፍ ጥበቃ፣ ህግ 2015 በክፍል 70 (10) (ሀ) ስር የቀረቡ መግለጫዎች]**

## <u>መረጃ ማስታወሻ - የሽግግር ዝግጅቶች</u>

## <u>ለአለም አቀፍ ጥበቃ (የስደተኛነት ሁኔታና ንኡስ ጥበቃ) እና የመቆየት ፈቃድ ላይ በሚገባ ማመልከቻ ላይ የሚኖር ምርመራና ውሳኔ ላይ የነጠላ ማመልከቻ አካሔድ መግቢያ</u>

**ይህ መግለጫ የሚያገለግለው ለመረጃና መመሪያ ብቻ ነው፡፡ ይህም ለህግ ምክር የማያገለግልና ለአለም አቀፍ ጥበቃ ሕግ 2015 ምንም አይነት ትርጉም የማይሰጥ ነው፡፡ ይህ ማስታወሻ በአለም አቀፍ ጥበቃ ህግ 2015 ስር በሽግግሩ ዝግጅት ከጉዳዮት ጋር ግንኙነት ባላቸው ዋና ዋና ምድቦች ላይ ያተኩራል፡፡ የሽግግር ዝግጅቱ ሊፈጸምበት በሚችል  ሁሉ  ሁሉም የሚቻሉ ሁኔታዎች   አያዳርስም፡፡  ሕግ በ2015 ውል ላይ የበለጠ ዝርዝር መረጃ ቢፈልጉና  ዓንቀጾቹ በእርስዎ ጉዳዮት ላይ አተገባበር የሚመለከት የሕግ ምክር ያግኙ፡፡**

**<u>የመረጃ ማስታወሻው ከመረጃ መጸሃፉ የተለየ ሆኖ በአንድ ላይ የሚነበብ ሲሆን ለአለም አቀፍ ጥበቃ (IPO 1) እና ለአለም አቀፍ ጥበቃ መጠይቅ ማመልቻ (IPO 2) አመልካቾች በአንድ ላይ የሚሰጥ ነው፡፡</u>**

## 1. መግቢያ

1.1 የአለም አቀፍ ጥበቃ ህግ 2015 (የ 2015 ህግ) የተጀመረው በፍትህና እኩልነት ሚኒስቴር (‹‹ሚኒስቴሩ››) አማካኝነት በ **ታህሳስ 31/2016** ነው፡፡ በዚህ ማስታወሻ፣ ይህ ‹‹የተጀመረበት ቀን›› ተብሎ ይጠቀሳል፡፡

1.2 ይህ የመረጃ ማስታወሻ በማመልከቻዎት ምርመራና ውሳኔ (የተወሰነ የሂደት ደረጃዎች ላይ) በአለም አቀፍ ጥበቃ (የስደተኛ ሁኔታና ንኡስ ጥበቃ ላይ) በአለም አቀፍ ጥበቃ ህግ 2015 በስቴቱ (አየርላንድ)

ከመጀመሪያው ቀን በፊት ላይ ዝርዝር የሽግግር ዝግጅቶችን ይሰጣል፡፡ እንዲሁም በመቆየት ፈቃድ ላይ የተወሰነ ዝርዝርን ይሰጣል፡፡

1.3 በሽግግር ዝግጅቱ ላይ መረዳት እንዲኖሮት የሚያገዝ ነው

- ከ የስደተኞች ማመልከቻ ኮሚሽነር ጽህፈት ቤ (ORAC) የተገኙ የተወሰኑ የስደተኛ ሁኔታና ንኡስ ጥበቃ ማመልከቻዎች እና

- ከ የስደተኞች ይግባኞች ፍርድ ቤት (RAT) የተገኙ የተወሰኑ የስደተኝነት ይግባኞች

ከ ታህሳስ 31/2016 በፊት የገቡ ማመልከቻዎች የአየርላንድ ዜግነት መስጠትና ፍልሰት አገልግሎት አለማቀፍ ጥበቃ ቢሮ በህግ 2015 ስር ሂደቱ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

1.4 አንድ ሰው ለስደተኛ መብት ማረጋገጫ ወይም ለንኡስ ጥበቃ እና ለአለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO) ማመልከት የሚያስችለው አካሄዶች ከዚህ ጋር በተያያዘው ለአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካቾችን (IPO 1) በሚመለከተው መጽሀፍ ላይ በዝርዝር ሰፍረዋል፡፡ መጽሀፉም በተጨማሪ እንደ አለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች የሚኖርቦትን መብቶችና ግዴታዎችን እንዲሁም በማመልከቱ ሂደት ከማን ጋር መነጋገር እንዳለብህም ይገልጻል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መጽሔቱ ከአለም አቀፍ ጥበቃ የተለዩ ከሚኒስቴሩ ሊታዩ የሚችሉ መነሻዎች ፈቃድ አሰጣጥምሰ ሂደቶችንም አካቷል፡፡

1.5 (IPO 2) የአለም አቀፍ ጥበቃ መጠይቅ ማመልከቻንም አያይዘናል፡፡

1.6 ማመልከቻዎትን ለመደገፍና **የ2015 ህግ የሽግግር ዝግጅት በእርሶ ላይ ተፈጻሚ የሚሆንበትን ነገር መረዳቶትን ለማረጋገጥ** የመረጃ ማስታወሻውንና የተያያዘውን የመጠይቅ መጻፍ በጥንቃቄ ማንበብ እንዲሁም አስፈላጊ ከሆነ የህግ ምክርን መሻት ሊያስፈልግ ይችላል፡፡

## 2. የአለም አቀፍ ጥበቃ ህግ 2015 ተግባር

2.1 የ 2015 ህግ በነጠላ የማመልት ሂደትን የአለም አቀፍ ጥበቃን ማግኘት የሚቻልባቸውን የአሰራር ሂደቶችን መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮች ማብራሪያ ይሰጣል (የስደተኛ ሁናቴና ንኡስ ጥበቃ) እና በአንድ ተከታታይ ሂደት በሌሎች ምክንያቶች በስቴቱ ውስጥ ለመቅረት ፈቃድ የሚሰጥበትን ምክንያት ያብራራል፡፡

2.2 የ2015 ህግ የሽግግር ዝግጅትን ለስደተኛ ሁኔታና ንኡስ ጥበቃ ላይ ለተወሰኑ አመልካቾች ብቻ የሚሰሩ አለም አቀፍ ማስተካከያዎችን ተግባራዊ ከሆነበት ቀን በፊት የተከናወኑትን ይዟል (**ክፍል 4 ይመልከቱ**)፡፡

## 3. በ2015 ህግ ስር የሆኑ ማመልቻዎች ይግባኞችን ወሳኝ ማነው?

3.1 2015 ህግ ስር ORAC ተወግዷል፡፡ ለአለም አቀፍ ጥበቃን ምርመራ ኃላፊነትንና በቀረቡ ማመልከቻዎች ውሳኔ አሰጣጥ እና ከዚህ ጋር የሚዛመዱ በዚህ መረጃ ማስታወሻ ሽፋን የተሰጣቸው የፈቃድ አሰጣጥ ሁኔታዎች ተግባራዊ ከሆነበት ቀን አንስቶ እና የ2015 ህግ የተደነገጉ ሁሉ ለ የአየርላንድ ዜግነት መስጠትና ፍልሰት አገልግሎት አለማቀፍ ጥበቃ ቢሮ (INIS) ተላልፏል፡፡

3.2 በ2015 ህግ ስር፣ RAT እንዲሁ ተወግዷል፡፡ የአለም አቀፍ ጥበቃን የሚመለከቱ ይግባኞችን ኃላፊነትና ውሳኔ ሰጭነት ተግባራዊ ከሆነበት ቀን አንስቶ የ2015 ህግ የሚመለከታቸው ድንጋጌዎች ለአለም አቀፍ ጥበቃ ልዩ ፍርድ ቤት (IPAT) ተላልፈዋል፡፡

## 4. ለስደተኛ ሁኔታና ለንኡስ ጥበቃ የሚረቡና <u>በእጅ ላይ</u> ያሉ ማመልከቻዎችን ከመጀመሪያው ቀን በፊት አይፈጸምም

4.1 በ EU ዱብሊን ደንብ ስር እና በተወሰነ አማራጭ ስምምነቶች መሰረት ማመልከቻው የማይታይ ከሆነ የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካቾችን በሚመለከተው (ስለ አለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻመጸሀፍ <u>ክፍል 10</u> ላይ የሰፈሩትን ይመልከቱ) የሚከተሉትን የሽግግር ዝግጅቶች ከትግባራዊ ቀን <u>በፊት</u> በቀረቡና በዚያ ዕለት ፍጻሜ ባላገኙ ለስደተኝነት ሁኔታና ንኡስ ጥበቃ በቀረቡ ማመልከቻዎች ላይ ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

### ምድብ 1 - ORAC የስደተኝነት ማመልከቻ

ከመጀመሪያ ቀን በፊት ካመለከቱና በስደተኛ ህግ 1996 ስር ORAC ሪፖርቱ ካልተዘጋጀ (በሌላ ቃላት ድጋፍ ካልተሰጠ) ማመልከቻህን ከአለም አቀፍ ጥበቃ የቀረበ ተደርጎ (ለሁለቱም የስደተኝነት ሁኔታና ንኡስ ጥበቃ) በ2015 አዋጅ ስር ይወሰዳል፡፡ <u>ለስደተኝነት ሁኔታ ወይም ንኡስ ጥበቃ ድንጋጌ መሆን አለመሆንህን ለመወሰን</u> ፋይሎት ለአለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ይተላለፋል፡፡

ለስደተኝነት ሁኔታ ወይም ለድጎማ ጥበቃ ብቁ ሆነህ ካልተገኘህ በሌሎች ምክንያቶች መቅረት የሚያስችልህን ፈቃድ ለመስጠት ሚኒስቴሩ በአፋጣኝ ይመለከተዋል፡፡ ይህ ውሳኔ የሚተላለፈው ባቀረቧቸው ወረቀቶች መሰረት ሲሆን አዲስ የመቅረት ጥያቄ ማመልከቻ እንዲያቀርቡ አትጠየቅም፡፡

**ምድብ 2- የስደተኝነት ይግባኝ**

ከመጀመሪያ ቀን በፊት የስደተኝነት ሁኔታ ይግባኝ ለ RAT ቀርቦ ግን በ RAT የቀን ውሳኔ  ያልተሰጠው ከሆነ  በ2015 ህግ ስር ለአለም አቀፍ ጥበቃ እንዲመለከትክ ይቆጠራል፡፡ ለንኡስ ጥበቃ ብቻ ብቁ መሆንን ለመወሰን ፋይሎት ለ IPO ተላልፏል፡፡ በእንዲህ ዓይነቶቹ ጉዳዮች ለስደተኝነት ብቁ መሆንህን በ ORAC የተሰጠህ ድጋፍ ይጠበቃል እንዳለም በቦታው ይቀመጣል፡፡ IPO የንኡስ ጥበቃ እንዳይሰጥህ ድጋፉን ከሰጠ በሌሎች ምክንያቶች  መቅረት ይችሉ እንደሆነ ሚኒስቴሩ ጉዳዩን በአፋጣኝ ይመለከተዋል፡፡ የቀደመው ይግባኝ ለ RAT የቀረበው ይጠበቃል ለአዲሱ IPO ተላልፏል፡፡ የንኡስ ጥበቃ ከነፈገህ የ IPO የድጎማ ጥበቃ  ድጋፍ ለ RAT ይግባኝ ማለት ትችላለህ  ሁለቱም ይግባኞች እንደ አንድ ተወስደው ሁለቱም ይደመጣሉ፡፡ በ IPO የመቅረት መብት ከተነፈግ  በ2015 ህግ ስር IPAT መሰረት ውሳኔ እንዲሰጥህ ውሳኔውን ይግባኝ ማለት እንደማይችሉ ማስታወስ ይኖርቦታል፡፡

**ምድብ 3- የድጎማ ጥበቃ**

ለንኡስ ጥበቃ ከመጀመሪያው ቀን በፊት ያመለከትክ ከሆነና በቀኑ ORAC ምርመራውን ያልጀመረ ከሆነ ማመልከቻዎትን በ2015 ህግ ስር ለአለም አቀፍ ጥበቃ የቀረበ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ሌሎች የንኡስ ጥበቃ ጉዳዮችን ብቻ ለመመልከት መቻሎትን ለማጤን ፋይሎት IPO ይተላለፋል፡፡ በእንዲህ ዓይነቶች ጉዳዮች የስደተኞች ድጋፍ ORAC የተሰጠ (ወይም በይግባኝ ላይ በ RAT የተሰጠውን ውሳኔ፣ ካለ) በቦታው ይቀመጣል፡፡

**ሌላ መረጃ**

(i) ከትግበራው ቀን በፊት በንኡስ ጥበቃ አመልክተው ከሆነና በ ORAC በቀኑ ማመልከቻውን መመርመር ከጀመረ IPO የ ORAC ስራ ከመውሰዱ በዘለለ በ2015 ህግ መሰረት ማመልከቻዎት አይተዳጎልም፡፡ ቀደም ሲል የነበሩ የህግ አተረጓጎሞች ቀጣይ ሆነው IPO ቀደም በነበሩ የህግ አካሄዶች ማመልከቻዎትን ይመረመረዋል፡፡

(ii) ለንኡስ ጥበቃ አመልክተው ከሆነ ተግባር ላይ ከሚውልበት ቀን በፊት ማመልከቻዎ ለ RAT ይግባኝ የተጠየቀበት ከሆነ በቀድሞ የህግ አፈታቶች መሰረት ይግባኝዎ ውሰኔ እንዲሰጥበት ለ IPAT ይተላለፋል፡፡

## 5. ሀገር ዉስጥ የመቆየት ፈቃድ

5.1 በ2015 ህግ ስር ለአለም አቀፍ ጥበቃ ያቀረቡት ማመልከቻዎ በ IPO ተቀባይነት ካጣ (የስደተኝነትና የድጎማ ጥበቃ ወይም የድጎማ ጥበቃ ብቻ ሊሆን ይችላል) በሌሎች ምክንያቶች በሀገሪቷ ውስጥ መቆየት መቻል አለመቻልዎን በተመለከተ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

5.2 የ2015 ህግ የሚሰራባቸው ሁኔታዎች እና አካሄዶች ተቀይረዋል ስለሆነም ሚኒስትሩ በስቴቱ ውስጥ ለምን መቆየት እንዳለብዎ ደብዳቤ ላይጽፍና ላይጋብዝዎ ይችላል፡፡ ይልቁንም የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎ ውድቅ ሲደረግ ውድቅ እንዲሆን ድጋፉን የሰጠ ከሆነ፣ ለ IPO ሊተላለፍ ይችላል፡፡ ውሳኔው የሚተላለፈው በእርስዎ ጉዳይ ላይ በቀረቡ መረጃዎችና ማስረጃዎች መሰረት ይሆናል፡፡

5.3 ስለሆነም የእርስ ጉዳይ በ2015 ህግ ስር ለአለም አቀፍ ጥበቃ የቀረበ ተደርጎ IPO ውሳኔ የሰጠበት ከሆነ ሀገር ውስጥ የመቆየት ፈቃድ ሊሰጠኝ ይገባል የሚሉባቸውን ምክንያቶች በአለም አቀፍ ጥበቃ መጠይቅ (IPO 2) የሰፈሩትን አግባብነት ያላቸው ምክንያቶችን በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርብዎታል፡፡ ለምሳሌ ቤተሰብዎና እና በሀገርዎ ውስጥ ያሉ ሁኔታዎች፣ ከሀገርዎ መንግስት ጋር ያለዎት ግንኙነት፣ ከስቴቱ ውጪም ሆነ ከግዛት ውስጥ ያልዎት ባህሪ እና ጸባይ ሰብአዊ ጉዳዮች ጠቀሜታ አላቸው፡፡
አስፈላጊ ለሚመለከት ዝርዝር ማብራሪያ ለማድረግ እባክዎን የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካቾች የመረጃ መጸሀፍ (IPO 1) ይመልከቱ፡፡

5.4 <u>በሂደት የሚኖሩ ጠቃ ለውጦችን (ለምሳሌ፣ ቤተሰብዎት ወየም የአካባቢዎትን ሁኔታ ወይም የመጡበትን ሀገር ሁኔታ) ለ IPO (በሚኒስቴሩ ስም)ማሳወቅ ይኖርቦታል፡፡</u>

**6. በሽግግር ዝግጅቱ ሽፋን የማገኝ ከሆነ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ሌላ ማመልከቻ ማስገባት ይኖርብኛል?**

6.1 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ያስገቡት ማመልከቻ ከላይ <u>በክፍል 4</u> ምድብ ስር ከተገለጹት ጋር ተመሳሳይ ከሆነ፣ ለሚኒስቴሩ አዲስ የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ማስገባት **አያስፈልጎትም** ነገር ግን ለአለም አቀፍ ጥበቃ መጠይቅ ማመልከቻ (IPO 2) <u>በክፍል 7</u> ስር ያሉ ጠቃሚ ክፍሎችን ይከተሉ፡፡

**7. የአለም አቀፍ ጥበቃ መጠይቁን ማመልከቻ ይሙሉ**

7.1 የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎት ከላይ <u>በክፍል 4</u> በመድብ 1፣ 2 ወይም 3 ስር የሚታይ ከሆነ፣ የአለም አቀፍ ጥበቃ መጠይቁን እንደሚከተለው ይሙሉ፡-

**ምድብ 1 ጉዳይ (የስደተኝነት ሁኔታ፣ ንኡስ ጥበቃና የመቆየት ፈቃድ)**

እባክዎን መጠይቁን **በአጠቃላይ** ይሙሉ፡፡

**ምድብ 2 ጉዳይ (ንኡስ ጥበቃ፣ የመቆየት ፈቃድ)**

እባክዎን መጠይቁን ይሙሉ ነገር ግን ከስደተኛ ሁኔታ ጋር የሚገናኘውን ክፍል አይሙሉ **(ጥያቄ 63ሀ እና 63ለ)**፡፡

**ምድብ 3 ጉዳይ (ንኡስ ጥበቃና የመቆየት ፈቃድ)**

እባክዎን መጠይቁን ይሙሉ ነገር ግን ከስደተኛ ሁኔታ ጋር የሚገናኘውን ክፍል አይሙሉ **(ጥያቄ 63ሀ እና 63ለ)**፡፡

7.2 የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎትን የሚደግፍ ተጨማሪ መረጃ **በጽሁፍ** ማስገባት ይችላሉ፡ ፡ ከማመልከቻዎት ጋር ግንኙነት ያለው አንዴ ያስገቡትን ሰነድ መልሶ ማስገባት አያስፈልጎትም ይህም በፋይሎት ውስት የሚገኝ በመሆኑ ነው፡፡

7.3 የአለም አቀፍ ጥበቃ መጠይቅ ማመልቻውን ለአለም አቀፍ ጥበቃና ለመቆየት ፈቃድ (ካለ) ጉዳዩ እንዲሄድ ከሚያግዞት ተጨማሪ መረጃ ጋር ይመልሱ፣ ይህም የሚሆነው ከታች በፖስታ ላይ በተገለጸው አድራሻ የመረጃ ማስታወሻ የያዘው ደብዳቤ በደረሶት **ከ 20 የስራ ቀናት ያልበለጠ** መሆን አለበት

Transitional Cases Section,

International Protection Office,

Irish Naturalisation and Immigration Service,

79 - 83 Lower Mount Street,

Dublin 2,

D02 ND99

7.4 **ከላይ በአንቀጽ 7.3 መረጃን ካስገቡ በኋላ እርሶ እና/ወይም የህግ አማካሪዎት ደጋፊ መረጃን ለ IPO የሚስገቡ ከሆነ፣ በቻሉት ፍጥነት ያድርጉ እንዲሁም፣ ማድረግ የሚችሉበት ሁኔታ ላይ ካሉ፣ ቃለመጠይቅ ከሚያደርጉበት ሁለት ሳምንት በኋላ አይሁን፡፡ ይህ የግዜ አስፈላጊ ከሆነ ሰነዱ እንዲተረጎም ለማስቻል ይረዳል እንዲሁም የ IPO ቃለመጠይቅ አድራጊው ከቃለመጠይቁ ቀን ቀደም ብሎ ሁሉም ወረደቀቶች እንዲኖሩትና እንዲያጤናቸው ያስችለዋል፡፡**

## 8. በአለም አቀፍ ጥበቃ ህግ 2015 ስር ቃለመጠይቅ የሚደረግልኝ መቼ ነው?

8.1 የአለም አቀፍ ጥበቃ መጠይቁን (IPO 2) ሞልተው በመለሱ ግዜ እንዲሁም በክፍል 7 መሰረት የሚያስፈልጉትን ደጋፊ መረጃዎች ካያያዙ፣ አስፈላጊ ሲሆን የአለም አቀፍ ጥበቃ ጽ/ቤት ያገኞታል፡፡ IPO ብዛት ያላቸውን ማመልከቻዎት ስለሚያስተናግድ ቃለመጠይቆት በርከት ላሉ ወራት በኋላ ቀጠሮ ሊያዝለት ይችላል፡፡

8.2 ቃለመጠይቅ ለማድረግ አለም አቀፍ ጥበቃ ጽ/ቤትን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ማግኘት **አያስፈልግም**፡፡

## 9. ይግባኙ በአይፒኤቲ የሚሰማው መቼ ነው?

9.1 ከመጀመሪያው ቀን ቀደም ብሎ ውሳኔ ያላገኙ የስደተኝነት ይግባኝ ካሎት፣ ፋይሎት ከላይ ወደተገለጸው IPO ክፍል 4 ይተላለፋል፡፡

9.2 ውሳኔ ያላገኘ የንኡስ ጥበቃ ላይ ይግባይ ካሎት፣ ይህ የሚሰማው በ IPAT ሲሆን የሚሰማበትን ቀን በ IPAT አማካይነት ይገለጽሎታል፡፡

## 10. ተጨማሪ መረጃ

10.1 በመረጃ ማስታወሻው ላይ በሚኖር ማንኛውም አይነት ጥያቄ በጽሁፍ ለCustomer Service Centre, International Protection Office, Irish Naturalisation and Immigration Service, 79-83 Lower Mount Street, Dublin 2 ወይም ለ info@ipo.gov.ie መቅረብ ይኖርበታል፡፡

10.2 የአለም አቀፍ ጥበቃ 2015 ህግ እና ህጋዊ ድጋፎችን በሙላ በ **www.ipo.gov.ie** ላይ ማግኘት ይችላሉ፡፡

10.3 ይህ የመረጃ ማስታወሻ በብዙ ቋንቋዎች ከላይ ባለው ኢሜል አድራሻ ማግኘት ይቻላል፡፡

10.4 ከአለም አቀፍ ጥበቃ ወይም ከመቆየት ፈቃድ ማመልከቻዎት ጋር በሚገናኝ ከ የህግ ድጋፍ ቦርድ ገልግሎትን ማግኘት ይችላሉ፡፡ በአማራጭነት፣ በራሶት ወጪ የግል ጠበቃ ማግኘት ይችላሉ፡፡

10.5 የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎትን በተመለከተ የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ማማከር ይችላሉ፡፡

10.6 በዚህ የመረጃ ማታወሻ የተገለጹትን ድርጅቶች ማግኛ **በቅጥያ 1** ላይ ማግኘት ይቻላል፡፡

**የአየርላንድ ዜግነት መስጠትና ፍልሰት**
**አገልግሎት አለማቀፍ ጥበቃ ቢሮ**
**አገልግሎት ጥር 2017**

## ቅጥያ 1

## የተወሰኑ የማግኛ ዝርዝሮች

**International Protection Office**
Irish Naturalisation and Immigration Service,
79-83 Lower Mount Street,
Dublin 2. D02 ND99
ቴሌፎን: 01 6028000
ፋክስ: 01 602 8122
ድረ ገጽ: www.ipo.gov.ie
ኢሜይል: info@ipo.gov.ie

**International Protection Appeals Tribunal**
6/7 Hanover Street
Dublin 2. D02 W320
ቴሌፎን: 01 474 8400
ሎ-ኮል፡ 1890 210 458
ፋክስ: 01 474 8410
ድረ ገጽ: www.protectionappeals.ie
ኢሜይል: info@protectionappeals.ie

**Legal Aid Board**
Legal Aid Board Law Centre - Smithfield,
48/49 North Brunswick Street,
Georges Lane,
Dublin 7. D07 PE0C
ቴሌፎን: 01 646 9600.
ድረ ገጽ: www.legalaidboard.ie
ኢሜይል: lawcentresmithfield@legalaidboard.ie

**International Organisation for Migration**
116 Lower Baggot Street,
Dublin 2. D02 R252
ነጻ ስልክ: 1800 406 406
ስልክ: +353 1 676 0655
ድረ ገጽ: www.ireland.iom.int
ኢሜይል: iomdublin@iom.int

**United Nations High Commissioner for Refugees (UNHCR)**
102 Pembroke Road,
Ballsbridge,
Dublin 4. D04 E7N6
ስልክ: 01 6314510
ኢሜይል: iredu@unchr.org